Amharic | አማርኛ

ጁላይ / ኦገስት 2026

homes victoria

BIG HOUSING BUILD

# ኖርዝ ሪችመንድ

## የማህበረሰብ ወቅታዊ መረጃ



## በኖርዝ ሪችመንድ በሚቀጥለው የመልሶ ማልማት ደረጃ ላይ የራስዎን አስተያየት ይስጡ

የእርስዎ አስተያየት ለወደፊቱ የንድፍ እና የእቅድ ሂደቱን በቦታው ላይ ለመቅረጽ ይረዳል።

የዳሰሳ ጥናቱን በ **engage.vic.gov.au/north-richmond-housing-precinct** ማጠናቀቅ ወይም የQR ኮድን ስካን ማድረግ ይችላሉ።

**የዳሰሳ ጥናት እሁድ ኦገስት 16 ከምሽቱ 11:59 ሰዓት/pm ላይ ይዘጋል።**

ወይም፣ በአንዱ ዝግጅታችን ላይ ይምጡ እና ቡድናችንን ያነጋግሩ።

**የማህበረሰብ በአካል ሊገኙባቸው የሚችሉ ክፍለ ጊዜዎች:-**
ዘ ለርኒንግ ባንክ/Learning Bank 124 Victoria St, Richmond
**ቅዳሜ ኦገስት 1 ከጠዋቱ 11 ሰዓት/am እስከ ከሰዓት በኋላ 1 ሰዓት/pm ሐሙስ ነሐሴ 6 ከሰዓት በኋላ 5 ሰዓት/pm እስከ ምሽቱ 7 ሰዓት/pm**

**የማህበረሰብ መሸጫ ሱቆች**
ሪችመንድ ትሬደርስ
**ማክሰኞ ጁላይ 28 ከጠዋቱ 11 ሰዓት/am እስከ ከሰዓት በኋላ 5:30 ሰዓት/pm**

የአከባቢው ነዋሪዎች በአካል ሊገኙባቸው የሚችሉ ክፍለ ጊዜዎች መረጃዎች እና ግብዣዎችን ያያሉ።

ቤቶች ቪክቶሪያ የአቦርጂናል እና የቶረስ ስትሬት ደሴት ነዋሪዎችን የምድሪቱ ባህላዊ ጠባቂዎች አድርገው ይቀበላሉ እና ያለፉትን እና የአሁኑን ሽማግሌዎቻቸውን እውቅና ሰጥተዋል እና ያከብራሉ።



## የነዋሪዎች ድጋፍ BBQ

**እሮብ ኦገስት 26፣ ከጠዋቱ 10 ሰዓት/am እስከ ከሰዓት በኋላ 2 ሰዓት/pm**
ኖርዝ ሪችመንድ የማህበረሰብ ማዕከል

- በኦንላይን መስመር ላይ ጥገናን ለመጠየቅ እገዛ ማድረግ
- ስለ myGov ድጋፍ ማድረግ
- በመብራት እና ጋዝ ሂሳቦችዎ ላይ እገዛ ማድረግ
- የቤትዎን ደህንነት ለመጠበቅ ጠቃሚ ምክሮች መስጠት
- ስለ ትልቁ የመኖሪያ ቤት ግንባታ የበለጠ ይወቁ

## ከዳቫል ጋር ይተዋወቁ - አዲሱ የመገልገያዎች/facilities አስተዳዳሪ

ዳቫል በአዲሱ የመገልገያዎች ስራ አስኪያጅነት ሚናው ለነዋሪዎች እውነተኛ ለውጥ ለማምጣት ከፍተኛ ፍላጎት አለው።

የሥራ ሚናው የጥገና ስራዎችን እና ተቋራጮችን በቦታው ላይ ለማስተዳደር መርዳትን ያካትታል እና ዳቫልን በአካባቢው በየቀኑ በእግር ሲጓዙ ያያሉ።

አሁን ዳቫል ያሉት ፕሮጀክቶች፣ በሪችመንድ አከባቢ ውስጥ ደህንነትን እና ምቾትን በማሻሻል ላይ ያተኮረ የነዋሪዎችን የመኪና ማቆሚያ ማሳደግ እና የህዝብ መብራትን ማሻሻልን ያካትታሉ።

ዳቫል በጥሩ ሁኔታ የተያዙ ቤቶችን እና የጋራ ቦታዎችን አስፈላጊነት ይገነዘባል።



"[የእኔ] የመጨረሻ ግቤ ነዋሪዎች በሚኖሩበት ቦታ ደህንነት፣ መከበር እና ኩራት የሚሰማቸው አካባቢ መፍጠር ነው።
- ዳቫል

ከማህበረሰቡ ጋር ጠንካራ ግንኙነት ለመፍጠርም ቁርጠኛ ነው።

የጥገና ጥያቄን በኦንላይን እንዴት ማስገባት እንደሚችሉ ለማየት **housing.vic.gov.au/online-services** ይጎብኙ ወይም **13 11 72** ይደውሉ።

## እንደተገናኙ መቆየት

**ተሳታፊ ለመሆን ከታች ያለውን ይጎብኙ:-**

**የምክክር አስተያየት**

**ወቅታዊ መረጃ ለማግኘት ይመዝገቡ**

ተሳታፊ  ሆኖ ለመቆየት ከታች ያለውን ይጎብኙ:-

homes.vic.gov.au/richmond-precinct



በማህበራዊ ሚዲያዎች ላይ **Homes Victoria** ብለው በመፈለግ ይከተሉን።

በቪክቶሪያ መንግስት የተፈቀደ እና የታተመ ፣ 1 Treasury Place, Melbourne። © የቪክቶሪያ ግዛት፣ ሆምስ ቪክቶሪያ፣ ጁላይ 2026። (HV020926)። በFinsbury Green, Melbourne Victoria, 3000 የታተመ።

More Homes For Victorians

VICTORIA State Government

# በሪችመንድ ውስጥ ምን እየሆነ ነው

## ጁላይ / ኦገስት 2026

### 139 ሃይት ስትሪት/Highett Street

**የመሬት ላይ አገልግሎቶችን መፈተሽ**

- ጥቃቅን የምርመራ ስራዎች እስከ ጁላይ/ኦገስት ድረስ ይካሄዳሉ
- ምንም መስተጓጎል አይጠበቅም

**ስራዎች**

- ከባዶ አፓርታማዎች እና ከውጭ ግድግዳዎች ውስጥ አንዳንድ ትናንሽ የቁሳቁሶች ናሙናዎችን መውሰድ
- በእያንዳንዱ ባዶ ወለል መጨረሻ ላይ የደህንነት በሮች ይገጠማሉ

### ተከራዮችን ወደ አዲስ ቤቶች ለማዛወር ድጋፍ

**ከጠዋቱ 10 ሰዓት እስከ ምሽቱ 4 ሰዓት**
**ከሰኞ እስከ አርብ**

ኖርዝ ሪችመንድ
የማህበረሰብ ማዕከል
110 Elizabeth Street/
ኤልዛቤት ስትሪት

### በግቢው ዙሪያ

**በግቢው ውስጥ ያለው ደህንነት**

- በሁሉም ሕንፃዎች ውስጥ ላሉ ነዋሪዎች አዲስ የመዳረሻ ፎብስ መሰጠት ቀጥሏል። ለበለጠ መረጃ የፎየር ፖስተሮችን ይመልከቱ

**የቅርጫት ኳስ ሜዳ ማሻሻያ**

- የማሻሻያ ስራዎች ሊጠናቀቁ ተቃርበዋል፣ ስለሆነም ኦገስት/ሴፕተምበር እንደገና ሊከፈት ይጠበቃል




### 106፣ 108፣ 110 እና 112 ኤልዛቤት ስትሪት/Elizabeth Street

**የወደፊት መልሶ ማልማት**

**የአየር ኮንዲሽነር መገጠሙ ቀጥሏል**

**የብስክሌት ማንጠልጠያ**

- በእያንዳንዱ ሕንጻ ግርጌ ላይ አዲስ የብስክሌት ማንጠልጠያ ተገጥሟል። እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ይከታተሉ።

**የእግረኛ መንገድ ሥራዎች**

- የመንገድ ማሻሻያ ስራዎች በጁላይ መጨረሻ በ112 ኤልዛቤት ስትሪት አካባቢ ይጀምራሉ።
- ስራዎቹ እርስዎ በቀላሉ ለመዞር እንዲችሉ ያሉትን መንገዶች ማስፋት እና መጠገንን ያካትታሉ።

በአዳዲስ ቤቶች ውስጥ ይመልከቱ

### 5 ሉዊስ ኮርት/Lewis Court እና 161 ኤልዛቤት ስትሪት/Elizabeth Street

144 አዳዲስ ማህበራዊ ቤቶች እና የማህበረሰብ ቦታዎች

**2025 ተጠናቅቋል - ተከራዮች አሁን ገብተዋል**

### ቸርች ስትሪት፣ ኤልዛቤት ስትሪት፣ አንደርሰን እና የዊሊያምስ ኮርት በእግር የሚወጡ ሕንጻዎች

**ስራዎች**

ባዶ የሆኑ በእግር የሚወጡ ፎቆችን በማፍረስ ቀጣዩን የመልሶ ማልማት ደረጃ ለመጀመር ስንዘጋጅ እንቅስቃሴ መጨመሩን ያስተውላሉ።

- በጣቢያው ወሰን ዙሪያ አጥር ተዘርግቷል
- ፖስታ ኦፊስ ሌን ተዘግቷል። የቪክቶሪያ ስትሪት መዳረሻ በሌኖክስ እና በቸርች ስትሪቶች በኩል ብቻ ነው
- የሰራተኞች መገልገያዎች በቦታው ላይ ይዘጋጃሉ
- አንዳንድ ጊዜ የግንባታ ተሽከርካሪዎችን እንዲሁም አንዳንድ አቧራዎችን፣ ጫጫታዎችን ወይም ንዝረትን ሊያስተውሉ ይችላሉ
- አንዳንድ ጊዜ በኤልዛቤት ስትሪት ላይ በእግረኞች ተደራሽነት ላይ ለውጦች ሊኖሩ ይችላሉ፣ እባክዎን ምልክቶችን ይከተሉ እና ደህንነቱ የተጠበቀ የእግረኛ ማቋረጫ ነጥቦችን ይጠቀሙ
- በአንደርሰን ኮርት እና በዊሊያምስ ኮርት ላይ ባለው የጣቢያው ወሰን ውስጥ ያለው የመኪና ማቆሚያ ተዘግቷል




## በአካባቢዎ በሚሰሩ ስራዎች ዙሪያ ደህንነትን መጠበቅ

የደረጃዎችን ደህንነት ለመጠበቅ እንደ ጫጫታ፣ አቧራ እና ንዝረት ያሉ ነገሮችን በመደበኛነት እንቆጣጠራለን።

**በአካባቢው መዛወር**

- ሥራ ከመጀመሩ በፊት አጥር ሁል ጊዜ በቦታው ላይ ይደረጋል
- በእግረኛ መንገዶች ወይም መንገዶች ላይ በሚደረጉ ለውጦች ዙሪያ ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ ለመንቀሳቀስ ሁል ጊዜ ምልክቶችን ይከተሉ
- እርስዎን ለመርዳት እዚያ ሲሆኑ የትራፊክ አስተዳደር ሰራተኞች መመሪያዎችን ይከተሉ

**ቁሳቁሶችን ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ ማስተዳደር**

- አደገኛ ቁሳቁሶችን ለማስወገድ እና ለማጽዳት ጥብቅ የደህንነት ደረጃዎች ሁል ጊዜ ይዘጋጃሉ
- አደገኛ ቁሶች ያሉባቸውን ቦታዎች ማስወገድ እንዲችሉ ምልክቶች ሁል ጊዜ ይኖራሉ
- ሰራተኞች መከላከያ ልብስ ለብሰው ሊመለከቱ ይችላሉ

**መዳረሻን ማቆየት**

- የአደጋ ጊዜ አገልግሎት ተደራሽ እንዲሆን በማንኛውም ጊዜ ይጠበቃል
- ተደራሽ የመኪና ማቆሚያን ጨምሮ ደህንነቱ የተጠበቀ የመኪና ማቆሚያ መዳረሻ መኖሩ ይቀጥላል

የእኛ ሥራ የሚመራው በመደበኛ የምክር ቤቱ የሥራ ሰዓት ነው፡-

| **ከሰኞ እስከ አርብ** | **ቅዳሜ** |
|---|---|
| ከ 7am እስከ 6pm | ከጠዋቱ 9 ሰዓት እስከ ምሽቱ 3 ሰዓት |

አንዳንድ ጊዜ ከእነዚህ ሰአታት ውጭ ለመስራት የምክር ቤት ፈቃድ ያስፈልጋል ነገርግን ይህ ከተከሰተ ነዋሪዎችን እናሳውቃለን።

ሁሉም ስራዎች የሚከናወኑት በከፍተኛ የደህንነት ደረጃዎች እና የህግ መስፈርቶች ነው።

ተጨማሪ መረጃ የሚፈልጉ ነዋሪዎች የአካባቢዎን የቤቶች ቢሮ ያነጋግሩ፡-

**1300 598 521**

**richmond.housing@dffh.vic.gov.au**

በቋንቋዎ ውስጥ መረጃን ጨምሮ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት የሚከተሉትን ይጎብኙ – **homes.vic.gov.au/information-in-your-language**

ለአጠቃላይ ጥያቄዎች የኢሜይል ኣድራሻ:

**enquiries@homes.vic.gov.au**